# ዘብሄረ ኢትዮጲያ ጥላሁን ነገሠ!

በ ዘካርያስ ጌታቸው

ነፍስ ከስጋ እና ከዚች ምድር ተለይታ ወደ ዘላለማዊው ቤቷ ስትሄድ፡ በስጋው ስንብት ላይ ነፍስ እዛፍ ላይ ሆና ስንብቱን ትታዘባለች ብለው ያወጉኝ በልጅነቴ ትዝ አለኝ።

በፋሲካ ማግስት በእለተ ሰኞ ነበር በአሉን ለማክበር ከሄድኩበት ገዳም ከሚጣቅ አማኑኤል የጉዞ መልስ፡ ከምነዳው መኪና ውስጥ ከነበረ ራዲዮ በወጣ መብረቅ በውስጡ ያለነው መንገድተኞች የተመታነው። ሉሉታው ቀለጠ መኪናው መናገር ባይችልም ባቅሙ ምልክቶችን ማሳየት የፈለገ ይመስል ነበር። ወደምንሄድበት ወደ አገረ መዲናዋ አዲስ አበባ እስክንደርስ ድረስ ከተማው የተወረረ፤ ህዝቡ በአስከፊ በሽታ የተያዘ ይመስላል።

መድረስ አትቀርም እና አዲስ አበባ እለተ ሰኞኝ እምታስተናግድ ሳይሆን ስራ እማይሰራበትን ቀነ እሁድን በድጋሚ ነይ ያለች ይመስላል። አዎ አገሬው ተደናግጦአል እናት ኢትዮጲያም ተከፍታለች። ምድርም የጀግናን ስጋ ለመቀበል እንተፍ እንተፍ እያለች ነው።

ዜና እረፍት በአለም ተሰተጋባ። ዜና እረፍት በሰው ልጆች ህይወት ጎዳና ላይ ባተኮሩ ዘፈኖች እየታጀበ ነበር በአየር ላይ ሲነጉድ የነበረው። ራዲዮ፤ ቴሌቭዥኑ እንዲሁም ስልኩ ያየር መስመሩን ተቆጣጠሩት። ዘመን አመጣሽ እነ ቴክስት እና ኢሜል ስራ በዝቶባችው በከፍተኛ ውጥረት ላይ ነበሩ። አዎ ዜና እረፍት ተተኪ የለሹን የጀግናውን የታላቁን አቀንቃኝ የድምፃዊ ዶክተር ጥላሁን ገሠሠን እረፍት በአለም አስተጋባች። አገረ ኢትዮጲያ ከነልጆቿ ተረበሸች ተከፋች።

ልጆች እስኪመጡ ዘመደ አዝማድ እስኪሰባሰብ ጀግናውን ለመሸኘት እለተ ሀሙስ ትጠበቅ ጀመር። ሀሙስ የቀናችን ቅዱስ ሰአቷ ሳትደርስ የአለም ፍፃሜ አስቀድሞ ቢመጣ ኖሮ ስንቱ ደስ ባለው። ሰማያዊ ሰማይ በሞቃታማ ፀሃይ በመታጀብ እለተ ሀሙስን ተቀበሉዋት። እኔም ቸሩ ፈጣሪ ፈቃዱ ሆኖ በዚች ቀን ታላቁን ኢትዮጲያዊ ለመሸኘት ከጠዋቱ ነበር በመስቀል አደባባይ የተገኘሁት። ሀዘን አይቼአለሁ በህይወቴ ግን ይህንን መሳዩን አላየሁም። ልጆች ሉሉ ሲሉ፤ አርበኛው ሲፎክር፤ ወጣቱ ኢትዮጲያ ኢትዮጲያ ሲል ከፊሉ ጥላሁን አልሞተም እያሉ ቦታውን ታላቅ እሳተ ጎመራ ያጥለቀለቀው አስመስለውት ነበር።

አንድ የሃይማኖት አባት እንዲህ ብለው ነበር "እሱ ሙሽራውን ዳረ፤ ወታደሩን አስታጠቀ ለተራበው አለሁልህ አለ። እሱ ሁሉን አድርጎ ወደጌታው ሄዶአል። ይልቁንስ ላንተ ምንም ላልሰራነው ብታለቅስ ይሻልሃል" አሉ። ታላቅ አነጋገር ነው ነገር ግን ለራሳችን ማልቀስ እናቅበት ይሆን? የጌታው አስክሬን በጦር ሰራዊት የማርሽ ባንድ ከቤቱ ታጅቦ መስቀል አደባባይ ደረሰ።

በብዙ መቶሺህ የሚቆጠሩ አፍቃሪዎቹ፤ የባለሞያ ጓደኞቹ ባለስልጣናትን ጨምሮ በነጎድጓድ ድምፅ ተቀበሉት። መስቀል አደባባይ ደመራን ላመቱ ለሁለተኛ ጊዜ እምታከብር ይመስል ነበር። እራሳቸውን በመሳት በድንገተኛ አደጋ መኪና የሚመላለሱ ተረጂዎች ይታያሉ። ይህች ታሪከኛ አደባባይ ለዘመናት እማይረሳ ታሪክ ለኢትዮጲያ ብቻ ሳይሆን ለሃገረ አፍሪካ አሳየች። የመስቀሉ አደባባይ መርሃ ግብር እንደተጠናቀቀ ጉዞው ሽቅቡን ወደ ቅድስተ ስላሴ ሆነ።

የአዲስ አበባን ህዝብ ለብዙ ወራቶች እያንገላታ የነበረው አልበገሩ ባይ የሐሩሩ ፀሃይ ማንንም አልበገረውም እንደውም የፀሃዩ ሃይል ታዳሚውን ጉልበትና ብርታት የሰጠው ይመስላል። አቀንቃኙን ንጉስ እምዬ ሚኒሊክ ቤተመንግስት ሠረገላው ጠበቀው። አገር ቀውጢ ሆነች። ተረግጠው እማያቁ መንገዶች ተረገጡ። ክብር ለታላቁ ጀግና ተሰጠ።

ለታሪካችን፤ ለማንነታችን ላልገዛ ባይነታችን መሰረትና ምሰሶ የሆነችው የኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን በጳጳሱ፤ በካህናቱ እንዱሁም በመዘምራን ታጅባ በአክብሮት የአገሪቱዋን ጀግና በደጃፏ ተቀበለች። ሁሉንም ነኪ ጥላችን ለውድ እናት አገራችው ከወራሪ ጠላት ሲከላከሉልን ከነበሩ አርበኖች እና ታላላቅ ኢትዮጲያኖች ወዳረፉበት ቦታ አመራ። ህዝብ ወንድሜን፤ መምህሬን፤ ጀግናዬን መሬት አላስገባም የሚል ይመስላል። ቅድስተ ስላሴ ከታላላቁ ነገሥታት ጀምሮ ያላየችውን ታሪክ አየች ግራም ተጋባች። **የወሊሶው ወጣት ያገር ፍቅሩ አቀንቃኝ ዘብሄረ ኢትዮጲያ ጥላሁን ነገሠ።**

አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ ተብሎ ተፅፎአልና እናት ኢትዮጲያ ውድ ልጅዋን ወደ አፈር መለሰች። የሁሉም ዘር አባት; የእስላሙ ወድም የክርስትያኑ ልጅ ወድማችን ጥላሁን ታዲያ እንደትረካው ነፍሱ ይህንን ታምር እዛፍ ላይ ሆና አይታው ይሆን?

ጥላችን ጥላሁን ላገሩ ዘመተ፤ ለተራበው ጩሳ እንዲሁም ለዘመኑ የተሰቦ በሽታ ምቀኝነትን፤ አላሰራ ባይነትን እንዲሁም ወሬን አወገዘ። ሰምተነው ይሆን? አዎ አይቀርምና ወድማችን አባታችን በእለተ ሐሙስ በሚያዛያ 15 ታሪክ ሰሪው እማይደገም ታሪክ አሳየን። የኛን እንጃ እንጂ እሱእንኳን አልሞተም።

ለሰው ልጅ አለሁልህ ማለት በቁመናው ነውና በህይወት ዘመኑ እያለ ከጎኑ ለቆማችሁ አይዞህ ላላችሁት እና ጊዜ ለሰጣችሁት እግዚአብሄር ዋጋችሁን ይክፈለው።



ነፍሱ በገነት ያኑርልን!

ዘካርያስ ጌታቸው።